# ዶ/ር አቢይና የፕሬስ ነጻነት በኢትዮጵያ

(ወንድወሰን ተክሉ-የኢትዮሚዲያ አምደኛ)

**መነሻ ጭብጥ-የዓለም የፕሬስ ቀን

ሰላም ጤና ይስጥልኝ ውድ እድምተኞቼ፤ እንደምን ሰንብታችኋል?

በየአመቱ ሚያዚያ ሶስት ቀን የሚከበረውን የዓለም ፕሬስ ቀንን መሰረት ያደረገው የዛሬው መጣጥፌ የሚያነጣጥረው በኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት ዙሪያ በተለይም ከአዲሱ ጠ/ም ዶ/ር አቢይ አህመድ መስተዳድር ላይ ያተኮረ ሆኗል፡፡

በዘንድሮው የዓለም ፕሬስ ቀን በዓል ሀገራችን ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ግዜ አንድም ጋዜጠኛ ወይም ጦማሪና ጸሃፊ በእስር ያልተገኙበት ወቅት የተከበረ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል ማለት ይቻላል፡፡ በእስር እየማቀቁ የነበሩትን አስራ ስድስት ጋዜጠኞች በቅርቡ (ከወራት በፊት) ከእስር በመፈታታቸው የተነሳ በአሁኑ ሰዓት አንድም ጋዜጠኛ በእስር ቤት እንደሌለ የተነገረላት ሀገራችን ኢትዮጵያ በጸረ ፕሬስ አቋሟ እንድትታወቅ ያደረጓትን ጨንቋኝ ህግጋቶቿን ገና ያልለወጠች በመሆኗ ዛሬም ስሟ በበጎ ሲነሳ አይታይም፡፡

ከሁለት ዓመት በፊት በመጀመሪያ በኦሮሚያ ቀጥሎም በአማራ የተነሳው ህዝባዊ እምቢተኝነት አመጽ ካነገባቸው ወሳኝና በርካታ ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ «የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ ይፈቱ» የሚል በመሆኑ ስርዓቱ ሳይወድ በግድ ከለቀቃቸው ከስድስት ሺህ በላይ የፖለቲካ እስረኞች ውስጥ አስራ ስድስቱ ጋዜጠኞችና ጦማሪዎች በመሆናቸው የዘንድሮው የዓለም ፕሬስ ቀን በተከበረበት እለት በኢትዮጵያ የታሰሩ ጋዜጠኞች እንደሌሉ ቢገለጽም ጋዜጠኞቹን አሳሰራ ብሎ ለእስር የዳረገቻው ጨቋኙ ህግ ግን እንዳለ ያለ መሆኑ ይታወቃል፡፡

አዲሱ ጠ/ም ዶ/ር አቢይ አህመድ በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ ባደረጉት ንግግር «ጽህፈት ቤታችሁን በውጭ ሀገር ያደረጋችሁ የዲያስፖራው መገናኛ አውታሮች (እነ ኢሳትና ኦ ኤም ኤን መሰል ማለታቸው ነው) በአዲስ አበባ ቢሮ ከፍታችሁ ስራችሁን መስራት ስለምትችሉ ወደ ሀገራችሁ ግቡ» የሚል መልእክት ያለው ጥሪ አድርገው ነበር፡፡ የጠ/ምኒስትሩ ጥሪና በጎ እይታ የሚመሰገን በጎ ጅምርና ቅን የሆነ አቋምና አመለካከት እንደሆነ እረዳለሁና ለዚህም አመለካከታቸው ያለኝን አድናቆት ሳልገልጽ ባልፍ ፍትሃዊነትን ከውስጤ ያባረርኩኝ ያህል ስለሚሰማኝ ማድነቄን እገልጻለሁ፡፡

ሆኖም ይህ የጠ/ምኒስትሩ ቅን አመለካከትና አቋም ከሀገሬ ይትበሃሎች ውስጥ አንደኛውን በተለይም «እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው» የሚለውን ግን እንዳስታውስና እንዳውጠነጥነው ያስገደደኝ እውነታ ይህን የጠ/ምኒስትሩን በጎና ቀና አመለካከትም ይሁን አቋምን በገሀድና በተጨባጭ ሁኔታ ማስተናገድ የሚችል ህግጋቶችንና የአሰራር ዘይቤዎችን ተቀይረው ማየትም ሆነ መስማት ያለመቻሌ እውነታ ነው፡፡

በጋዜጠኞቹና ብሎም በተወሰኑ (ዛሬም ጭምር አቶ አንዳርጋቸው ጽጌን ጨምሮ ቢያንስ ቢያንስ ከአስር ሺህ የማያንሱ የፖለቲካ እስረኞች በመላ ሀገሪቱ እስር  ቤቶች ውስጥ እየማቀቁ እንዳሉ መረጃዎች ያመላክታሉ) የፖለቲካ እስረኞች መፈታት የተደሰተውና

የተስማማም የሚመስለው የዶ/ር አቢይ አመራር በእርግጥ ከባህር ማዶ ያሉትን የኢትዮጵያ ሚዲያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት ችለው በነጻነት የጋዜጠኝነት ሙያቸውን እንዲሰሩ ይፈቅዳሉን? የሚል ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ለመፍቀድስ ይቻላቸው ይሆንን ስል እራሴንና የዶ/ሩን የማስፈጸም አቅም፣ኋይልና የፖለቲካ ቁርጠኝነትን/Political will / መጠየቄና መመርመሬ አልቀረም፡፡

ጠ/ም ዶ/ር አቢይ አህመድ በውጭ ላሉት የኢትዮጵያዊያን መገናኛ ብዙሃን ተቋማት ያደረጉትን ጥሪ በደስታ ብቀበለው እንደ እኔ እንደ እኔ ግን ጠ/ምኒስትሩ ያንን የቃል ጥሪያቸውን ከማስማታቸው በፊት በሀገር ውስጥ ያሉትን የፕሬስ ተቋማትና ባለሙያዎቻቸውን እንዳይሰሩ ያገዳቸውን ጨቋኙን የፕሬስ ህግና የሽብር አዋጁን በማንሳት በእርግጥም ጋዜጠኞች በነጻነት እንዲሰሩ በማድረግ ብቻ የውጪዎቹን በቃል ሳይሆን በተጨባጭ ተግባር አሳምነው መጥራት ይቻላቸዋል ብዬ አምናለሁ፡፡

**በኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት እና የዶ/ር አቢይ አስተዳደር ሁኔታ-

በዘንድሮው የCPJ መቀመጫውን ኒው ዮርክ ያደረገ የጋዜጠኞች መብት ተማጓች ድርጅት ፣በRSF ድንበር የለሹና መቀመጫውን ፓሪስ ላይ ያደረገው የጋዜጠኞች መብት ተማጋች ድርጅትና መቀመጫውን ለንደን ያደረገው የArticle 19 ወይም አንቀጽ 19 የጋዜጠኞች መብት ተማጋች ድርጅቶች የ2017 ዓመታዊ ሪፖርት መሰረት ኢትዮጵያን ከግብጽና ከኤርትራ ቀጥላ በጸረ ፕሬስ ህጋጋቶቻና በጸረ ጋዜጠኞች እርምጃዋ ከአፍሪካ ሶስተኛዋ ጨቋኝ ሀገር አድርገዋታል፡፡

በኢህአዴግ አገዛዝ ስር ባለችዋ ኢትዮጵያ የፕሬስ ነጻነት በ1987ዓ.ም ከጸደቀው ሕገ መንግስት በፊት ቀደም ተብሎ በ1984ዓ.ም የጸደቀባት ሀገር ብትሆንም ከሃያ አምስት ዓመታት ቆይታ በኋላ የፕሬስ ህጉ ተሻሽሎና ተስተካክሎ በርካታ የፕሬስ ውጤቶችን ማፍራት የቻለ ሁኔታን መፍጠር የቻለ መሆን ሲገባው በተቃራኒ ሁኔታ ቁልቁል እንደካሮት ወርዶ ዛሬ በሀገራችን አንድም የፕሬስ ውጤቶች እማይታዩበት ሁኔታ ላይ መሆናችን እማይካድ እውነታ ነው፡፡

መልካም አስተዳደር፣የህግ የበላይነት የሰፈነበት፣በህግ ሁሉም እኩል ተጠያቂ የሆነበትንና ዲሞክራሲያዊ ተቋማት የተስፋፉበትን ስርዓት ለመገንባትና ብሎም ለማጎልበት ከሁሉ በፊትና ቀዳሚው ነገር የዜጎች ሀሳብን በነጻነት የመግለጽን ተፈጥሮዓዊ የሆነን መብት ማስከበርና ማክበርን ይጠይቃል፡፡

በፈረንጆቹ Freedom of Expression /ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ተብሎ የሚገለጸውና በመንግስታቱ ድርጅት እንደ የድርጅቱ ዋና ዋልታ ህግ ሆኖ ተቀባይነትን ያተረፈውን መብት ለጋዜጠኛውና ለፕረሱ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ ማህበረሰቡም የተገባ ተፈጥሮዓዊ መብት መሆኑን አምና ያልተቀበለች ወይም አምና ያላከበረችና ያላስከበረች ማንኛዋም ሀገር ስለ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት እናገራው ብትል ከቶም የሚቻላት አይሆንም፡፡

በሀገራችን ያለው የፕሬስ ነጻነትና አደረጃጀት ቅድመ የህወሃት ለሁለት መሰንጠቅ ወይም ቅድመ 1997ቱ ምርጫና ድህረ 1997ቱ ድህረ ምርጫ በሚልና በግርድፉ ለሁለት ተከፍሎ የሚታይ ክስተት እንዳለው ይታወቃል፡፡

በ1993ቱ የህወሃት ለሁለት መሰንጠቅ ማግስት አሸናፊ ሆኖ የወጣው የአቶ መለስ ቡድን በራሳቸው አቶ መለስ «የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቀጣይ 20ዓመት ፕሮግራምና የስራ እቅድ» በሚል ማንፌስቶው ባወጣው እቅድ ዘግየት ብሎ በ1997ቱ ምርጫ ማግስት የተገበራቸውን ፍጹም አምባገነናዊ የፕሬስ መጨቆኛ ህግጋቶችን በይፋ አስቀምጦ ነበር፡፡

እንደ የ1993ቱ የአቶ መለስ አብዮታዊ ዲሞክራሲ የመጪው 20ዓመት መርህና የስራ ፖሊሲ በሚዲያው ዓለም ውስጥ በኢትዮጵያ ምድር ጋዜጠኛ የሚባለውን ባለሙያ አይነትና የስራ ድርሻን ቁልጭ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ ያም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የሚያፈራቸው ጋዜጠኞች ልማታዊ ጋዜጠኞች የሆኑና የአብዮታዊ ዲሞክራሲን አይዲኦሎጂ እሲበቃቸው ጠጥተው እነሱም በተራቸው ሰፊውን ህዝብ ነጋ ጠባ የሚግቱት ናቸው ሲል ያስቀምጣል፡፡ እያንዳንዳን ዜና፣ቃለ መጠይቅ፣ተከታታይነት ያላቸውን ፕሮግራሞችና ትንተናዎች ሁሉ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አይዲኦሎጂና መስመር ቅኝት የተቀኙ በአይዲኦሎጂው ዜማ የሚያንጎራጉሩና ብሎም እያንዳንዷን ዝግጅታቸውን በዚሁ አይዲኦሎጂ ሳንሱር አድርገው የሚያቀርቡት ብቻ ናቸው ጋዜጠኞች የሚባሉት ሲል በድፍረትና በማን አለብነት ሀገራችን የካድሬዎች መፈንጫ እንድትሆን አስፍሮ አልፏል፡፡

ይህ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ጋዜጠኞችና የፕሬስ አይነቶች ተብሎ በአቶ መለስ በ1993ዓ.ም ላይ የወጣው ፖሊሲ በድህረ 1997ቱ ምርጫ የተተገበረውና የቀረውን እንጥፍጣፊ የፕሬስ ህልውናን ጠራርጎ ያጠፋው፡፡

ይህ የአቶ መለስ አብዮታዊ ዲሞክራሲና ጸረ ፕሬስ አቋምና ህግጋቶቹ በሙሉ አቶ መለስ ቀደም ብለው በፕሬሱ ላይ ያላቸውን ለከት የለሽ ጥላቻና የጠላትነት መንፈስን ባሳዩበት የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የ20ዓመት መመሪያ ላይ የሰፈረ ሲሆን ይህም ሰውዬው በ1989 ላይ ሪፖርተር ጋዜጣ በተቋቋመበት ወቅት «በእነዚህኞቹ ፕሬሶች /ነጻውን ፕሬስ ማለታቸው ነው/ ከርሰ መቃብር ላይ እውነተኞቹ ፕሬሶቹ ያብባሉ » ብለው የፎከሩትን ፉከራ በእርግጥም አጠቃላይ የነጻ ፕሬሱን ውጤቶች ከእነ ማህበሩ ማለትም የኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞች ማህበር (ኢነጋማ )ጋር ጠራርገው በማጥፋት የራሳቸውን ፕሬሶች የፈጠሩበትን ሁኔታን እናስታውሳለን፡፡

ዛሬ ዶ/ር አቢይ ሊ/ር ሆነውበት ለሀገር ጠ/ምኒስትርነት የበቁበት ገዢው ድርጅታቸው አጠቃላይ የኢትዮጵያዊያኑን ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽን መብትFreedom of Expression / ያልተቀበለ ብቻ ሳይሆን በዚህ ዘርፍ የተሰማሩትን የነጻ ፕሬስ ውጤቶችንና ባለሙያዎቹን በጠላትነት የፈረጀ ድርጅት ሲሆን በዚህ አቋሞቹም እንደነ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋን በዚህ እኔ አምደኛ በሆንኩበት ኢትዮ ሚዲያ ድረ-ገጽ ላይ ባሳተመው መጣጥፍ ምክንያት ብቻ በአሸባሪነት ክስ የ18ዓመት እስራትን ከስድስት ዓመታት በፊት ፈርዶበት እንደነበረ ይታወቃል፡፡

እስክንድር በወቅቱ «ምኒልክ፣አስኳል፣ታሪክና» መሰል የህትመት ስራዎቹ በሙሉ ታግዶበትና ሀሳቡን የሚገልጽበት አንዳችም ነጻ የህትመት ውጤቶች በሌሉበት ሁኔታ ላይ መሰረቱን በአሜሪካን ሲያትል ባደረገው የኢትዮ ሚዲያ ድረ -ገጽ ላይ መጣጥፎቹን ለማቅረብ የተገደደበት ወቅት ሆኖ ሳለ ስርዓቱ ግን ያንንም በባህር ማዶ የሚታተምን

ድረ-ገጽ ላይ ሀሳቡን ማንሸራሸሩን እንደ አደጋና እንደ ስጋት በመቁጠር ጋዜጠኛውን እስከወዲያኛው ድረስ ከሙያው ለማገድ ሲል በአሸባሪነት ክስ የ18ዓመት ፖለቲካዊ ፍርድ ሊያስተላልፍበት እንደበቃ እንረዳለን፡፡

ሆኖም ምስጋና ለህዝባዊው እምቢተኝነትና ትግልThanks too the resistance and social disobedience of Ethiopian people who demanded the freedom of all political prisoners unconditionally, Eskinder is now a free man after 6 + years of incarceration ዛሬ መነፈስ ጠንካራው እስክንድር፣ተመስገን ደሳለኝና መሰል ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ለመፍታት በበቁበት ንቅናቄ የለውጥ ኋይልና ሞተር የሆኑት አቶ ለማ መገርሳና የቲማቸው አባል የሆኑት ዶ/ር አቢይ አህመድ ወደ ስልጣን መምጣት መቻላቸውን እያስተዋልነው ያለ እውነታ ነው፡፡

**ዶ/ር አቢይና የፕሬስ ነጻነት በሀገራችን-

በትንሹ ከስምንት ሺህ በላይ ታላቅ መስዋእትነትን (ከኦሮሚያ ከስድስት ሺህ በላይና ከአምሃራ ከሁለት ሺህ በላይ ወጣቶችና ንጹሃን በተሰውበት)ባስከፈለው ህዝባዊው እምቢተኝነት ትግል  የለውጥን ሀሳብ በማቀንቀንና ብሎም የህዝቡን ጥያቄ መመለስ አለበት በሚል ጽኑ አቋማቸው ወደ ጠ/ምኒስትርነቱ ስልጣን የመጡት ዶ/ር አቢይ አህመድ በእርግጥም ለመፈጸም ቃል የገቧቸውንና የተነሱበትን ዓላማ ለመፈጸም የነጻ ፕሬስ ህልውና እውን መሆንና የአጠቃላዩ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ተፈጥሮዓዊ መብት Freedom of Expression መከበር በእጅጉ ከሚያስፈልጋቸው ወገኖች ውስጥ እሷቸውና የተነሱለት ዓላማ እንደሆነ በግልጽ መረዳት ይቻላል፡፡

ጠ/ምኒስትሩ በእርግጥም የሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትና ብሎም የዚህ ጽንሰ ሀሳብ ልጅ የሆነው የነጻው ፕሬስ ህልውና በብቃትና በጥንካሬ እውን መሆንን ከማንኛችንም ይበልጥ እንጂ ባነሰ ደረጃ አይፈልጉም ያሰኙኝ እውነታዎች ጠ/ምኒስትሩ ለመፈጸም ቃል የገቡትንና በህዝባዊው ተቃውሞ ተደጋግሞ ሲጠየቅ የነበረውን የፖለቲካ ምህዳሩን የማስፋት፣የህግ የበላይነትን እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ፍትሃዊ የሀብት ክፍፍልን ለማረጋገጥና አላግባብ በስልጣን ተጠቅሞ የህዝብና የሀገርን ሀብት መዝረፍን ለመዋጋት ከጎናቸው ሊሆን ከሚገባው ህዝባዊ ኋይል ውስጥ ዋነኛው የጠንካራ ፕሬስ ተቋማት ህልውና መረጋገጥ እንደሆነ እሳቸውም ሆነ እሳቸውን መሳይ አማካሪዎቻቸው የሚስቱት ነው ብዬ ለማሰብ እቸገራለሁ፡፡

የዶ/ሩ አነሳስና አመጣጥ በጭቆና የታመቀውን ህዝብ አመጽ በማብረድ ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማስፋት እስከሆነ ድረስ የዲሞክራሲ መሰረትና ምሰሶ የሆነውን ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ተፈጥሮዓዊ መብትን ተቀብሎ ማስተናገድና ብሎም መጠበቅ እንመሆኑ መጠን ጠ/ምኒስትሩ ድርጅታቸው ኢህአዴግ የተጋዘበትን እና እራሱንና ሀገሪቷን ለአደጋ የዳረገበትን የጭቆን አገዛዝና ስልት ለመቀየር እስከመጡ ዘንዳ የመጀመሪያ ፍልሚያቸው የሚሆነው የእነዚህን እሴቶችን አጋጅና ከልካይ የሆኑትን ጨቋኝ ህግጋቶች ጋር በማድረግ መዱውንና አየሩን ለሁሉም ተጫዋች ነጻና ምቹ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የዚህ ዓላማ ባለቤት ባይሆኑ ኖሮ ጠ/ምኒስትሩ ለአፍ ያህል በውጪ የምትኖሩ ኢትዮጵያዊያን የመገናኛ ብዙሃን ባለቤቶች ወደ ሀገራችሁ ገብታችሁ ቢሮዋችሁን በአዲስ

አበባ በመክፈት በነጻነት መስራት ትችላላችሁ የሚለውን ጥሪ በድፍረት ይፈጽማሉ ብዬ ለማመን ይከብደኛል፡፡

ድርጅታቸው በጠላትነት የፈረጀው ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትና የነጻ ፕሬሱን ህልውና በሀገራችን እውን ለማድረግ የድርጅታቸውን ህግ ቀድመው መሻር ይገባቸዋል፡፡ ያንን ለመፈጸም የሚያስችል ህዝባዊ ኋይልና ድጋፍ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ ጋር የያዙ መሪ እንደመሆናቸው መጠን የመፈጸም ፍቃደኝነቱ እሷቸው ዘንድ እስካለ ድረስ የሚገጥማቸው ቅዋሜ ከህወሃቶች በኩል የሚያሰናክላቸው ኋይል ይሆናል ብዬ ማመኑ ይከብደኛል፡፡

የአራባ ሚሊዮን ህዝብ ባለቤት የሆነችው ጎረቤታችን ኬኒያ ከሃያ በላይ የግል ቴሌቪዥንና ራዲዮ ጣቢያዎችን በነጻነት ስታስተናግድ ጋዜጠኞቻንም ባለማሰርና የመረጃ ፍሰት ነጻነትን በማክበር በእጅጉ ትታወቃለች፡፡ ሀገራችን ከመቶ ሚሊዮን ህዝብ በላይ መኖሪያና የአፍሪካ ህብረት ዋና መቀመጫም ሆና ሳለ እስከዛሬ ድረስ አንድም የግል ቲቪ እና ራዲዮ ጣቢያ የሌላት ሲሆን በቅርቡ ንብረትነታቸው የህወሃት የሆኑ ቲቪና ራዲዮ ጣቢያዎች በግል ስም ተከፍተው እንዳሻቸው የሚሆኑባት ሀገር ነች፡፡

እንግዲህ አዱሱ ጠ/ምኒስትር ዶ/ር አቢይ አህመድ የፕሬስ ነጻነትና የሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ተፈጥሮዓዊ መብት መከበር ህዝባዊው እምቢተኝነት ካነሳቸው ጥያቄዎች ውስጥ አንጹና ዋነኛው እንደመሆኑ መጠን ከወዲሁ ሁኔታዎችን አመቻችተው እውን ማድረግ ካልቻሉ ለራሳቸውም ሆነ ለፓርቲያቸውና ብሎም ለህዝባቸው እማይገለጽ ችግር እንደሚፈጥሩ ይረዳሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለማጠናከርና ለማስፋፋት ወሳኝና ቁልፉ የሀሳብን በነጻነት የመግለጽን መብት ማስተናገድ፤ማስከበርና መከላከል እና የፕሬስ ነጻነት እውን ማድረግ ግዴታ ሲሆን ዲሞክራሲን ያለፕሬስ ማስብም ሆነ መግለጽ በጨለማ ውስጥ ያሉ ሁሉ ጥንዶች እርስ በርስ መጠቃቀስ ያህል ነው፡፡
ቸር እንሰንብት!!

---------------

አስተያየታትና ጥያቄያችሁን በteklu7@gmail.com ጻፉልኝ እመልሳለሁ